## በፍርድ ጉዳይ ላይ የቀረበ ትችት

## ከጋብቻ ውጪ ወይም ከጋብቻ ውጪ ከሚገኝ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኑሮ ውጪ የሚወለድ ልጅን አባትነት ስለማወቅ

መስፍን ገ/ ሕይወት

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

1. ከሳሽ አየለች ወ/ገብርኤል ተከሳሽ ጥሩነሽ ተሰማ

2. ከሳሽ ታደሰ ጉርሙ ተከሳሽ ጥሩወርቅ ኢየሱ

(የፍትሐብሔር መዝገብ ይግባኝ ቁጥር 394/72 እና 111/74 በተከታታይ)

ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአየለችን ጉዳይ [1] በተመለከተ በሰጠው ውሳኔ በአንድ የትምህርት ቤት መዝገብ ውስጥ በትምህርት ቤቱ ባለሥልጣን የሠፈረ ጽሑፍ አስመዝጋቢው ሰው ተመዝጋቢው ተማሪ ልጁ ነው ሲል በሰጠው የቃል መግለጫ ላይ የተመረኮዘ ከሆነ በአንቀጽ 748/ [2] በመመሥረት ይኸው ጽሑፍ ዋጋ ያለው የአባትነት ማወቅ ነው ሲል ወስኗል ። በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ በታደሰ ጉርሙ ጉዳይ ላይ በሰጠው ውሳኔ በዚሁ አንቀጽ ትርጉም መሠረት በጉዳዩ ውስጥ የተመለከተውን ልጅ ለማዋለድ የተደረገውን ክፍያ የሚያሳዩ በአንድ የሆስፒታል ገንዘብ ተቀባይ አባት ነው በተባለው ሰው ስም የተሰጠ የክፍያ ደረሰኝ እንደዚሁ ዋጋ ያለው የአባትነት ማወቅ ነው ሲል ወስኗል ። የትችታችን ዓላማ ፍርድ ቤቱ ከላይ እንደተጠቀሰው በመወሰኑ በፍሬ ነገር ግምገማም ሆነ በህግ አተረጓጐም ረገድ የፈጸመውን ስህተት ለማሳየት ነው ።

እንደ ፍርድ ቤቱ አባባል በአንቀጽ 748/1/ [3] ውስጥ የተመለከተው በራሱ በጸሐፊውም [4] ሆነ በሌላ ሰው የተዘጋጀ ማናቸውም " ክብደት ያለውና በጽሑፎቹ የተደረገ አስተማማኝ ማስረጃ " ነው ። ከዚህ አጠቃላይ መንደርደሪያ በመነሳት ፍርድ ቤቱ የሚከተሉትን የአባትነት ዝምድናን በአባትነት ማወቅ ለመመሥረት በቂ አድርጎ ተቀብሏል ።

1/ አባት ነው በተባለው ሰው በፍርድ ቤት ፊት ተሰጥቶ በፍርድ ቤቱ ጸሐፊ የተመዘገበ የምስክርነት ቃል ፤

2/ አባት ነው በተባለው ሰው መግለጫ ላይ በመመርኮዝ በመንግሥት ባለሥልጣኖች የሠፈረ ማናቸውም ጽሑፍ ወይም ቃለ ጉባኤ ፤

3/ ለማናቸውም መሥሪያ ቤት [5] አባት ነው በተባለው ሰው የተጻፈ ማናቸውም ማመልከቻና ፤

4/ ማናቸውም አባት ነው በተባለው ሰው ለዘመድ ወይም ለጓደኛ የተጻፈ የግል ደብዳቤ ።

ፍርድ ቤቱ በአየለች ጉዳይ የትምህርት ቤቱን ጸሐፊ እንደዚሁም በታደሰ ጉርሙ ጉዳይ የሆስፒታሉን ገንዘብ ተቀባይ እንደገለልተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በመቁጠር የትምህርት ቤቱን መዝገብና የሆስፒታሉን ደረሰኝ የአባትነት ማወቅ በትክክል የተደረገባቸው የማስረጃ ሰነዶች አድርጎ ወስዷቸዋል ።

አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ መሆን እንዳለበት አንቀጽ 748/1/ ውስጥ የተደነገገው ከሚገባው በላይ ላልቶ ተተርጉሟል። እንዲያውም “ ክብደት ያለውና በጽሑፍ የተደረገ አስተማማኝ ማስረጃ ” የሚሉት ቃሎች ከሚጠቀሙት ሀሳብ ይበልጥ ላልቷል ። የዚህን አባባል ትክክለኛ መሆን ወይም አለመሆን ከመመልከታችን በፊት የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተመሠረተበት ማስረጃ በህጉ መሠረት የታዘዘውን ፎርም (ዓይነት) ይዟል አልያዘም የሚለውን ወደጐን በመተው የዚሁኑ ማስረጃ በቂነት መገምገሙ ተገቢ ይመስለናል ።

## <u>የፍርድ ቤቱ የፍሬ ነገር ግምገማ</u>

በአየለች ጉዳይ ይግባኙ የቀረበው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ አቶ ወ/ገብርኤል ተ/ማርያም በእርግጥ የአየለች አባት መሆናቸውን አያሳይም በማለት ለመልስ ሰጭዋ የፈረደውን ፍርድ በመቃወም ነው።[6] ከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔውን የሰጠው ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ላይ በመመርኮዝ ነው ። በይግባኝ ክስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይዋን እንደ ልጅ መታወቅዋን በምስክሮች እንድታረጋግጥ በመፍረዱ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በአንቀጽ 748/2/ መሠረት ሕግ ወጥ ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮታል ። ከዚያም ፍርድ ቤቱ አንቀጽ 747/1/ን በመተርጐም ከዚህ በፊት ወደተጠቀሱት ውሳኔዎች ላይ ደርሰዋል ።

እስቲ አሁን ፍርድ ቤቱ የተቀበለውን ማስረጃና አያይዞም ያደረገውን ግምገማ በመጠኑ ጠለቅ ብለን እንመርምር ። የአባትነት ማወቅን ለማረጋገጥ የቀረበው ማስረጃ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ መልስ የሚሆን በቀለመወርቅ ት/ቤት የተጻፈ አየለች ወ/ገብርኤል በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከ1974 እስከ 1979 ድረስ ተማሪ እንደነበረችና የተመዘገበችውም በአቶ ወ/ገብርኤል ተ/ማርያም ማለትም በዚያን ጊዜ የትምህርት ቤቱ ሠራተኛ በነበሩና ራሳቸውን የልጅቷ አባት አድርገው ለትምህርቱ ባለሥልጣኖች በገለጹት ሰው ጥያቄ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ነው ። ከደብዳቤው በግልጽ እንደሚታየው አባት ነው በተባለው ሰው “ በጽሑፍ ” የተዘጋጀ ስላልነበረ ደብዳቤው ራሱ እንደ አንድ በጽሑፍ እንደሠፈረ የአባትነት ማወቅ መግለጫ ሊወሰድ ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱ ይኸው መግለጫ በእርግጥ በትምህርት ቤቱ መዝገብ ላይ ለመስፈሩ ደብዳቤውን እንደ ማረጋገጫ ወስዶታል ። ሆኖም ፍርድ ቤቱ የትምህርት ቤቱ መዝገብ ስላልቀረበለት [7] የትምህርት ቤቱን ጸሐፊ አቶ ማርቆስ ደልማን እንደምስክር ጠርቷል ። ፍርድ ቤቱ ምስክሩን የጠራበትን ምክንያት እንደሚከተለው ገልጾታል ።

> የትምህርት ቤቱን ባለሥልጣን የጠራንበት ምክንያት በራሱ በአባትነት ማወቅ ጥያቄ ላይ እንዲመሰክሩ ሳይሆን <u>በትምህርት ቤቱ መዝገብ ላይ በእርግጥ ምን እንደሰፈረ ፣ ስለአመዘጋገቡ ሁኔታና ትምህርት ቤቱ በምዝገባ ወቅት የሚከተለውን ሥርዓት እንዲያስረዱን በማለት ነው ።</u> (ለማትኮር የተሠመረው ተጨማሪ ነው ። —

በምስክርነት ቃላቸው አቶ ማርቆስ በትምህርት ቤቱ መዝገብ አየለች ወ/ገብርኤል የሚል ስም የሠፈረ መሆኑን ፣ ምዝገባውም የተካሄደው የልጅቷ አባት

* መ.ገ.ሕ. የሚለው የዚህ ፍርድ ጉዳይ ትችት አቅራቢን መስፍን ገ/ሕይወትን ይጠቁማል /ከመጽሔቱ አዘጋጅ/

ነኝ ብለው በገለጹት በአቶ ወ/ ገብርኤል ተ/ማርያም ጥያቄ መሆኑ ( ምናልባትም ግምት ላይ መድረስ ከተቻለ) በዚህ ጉዳይ ውስጥ ያለችው ይግባኝ ባይ በእርግጥም በመዝገቡ ውስጥ ስሟ ሰፍሮ የምትገኘው ልጅ መሆኗን ገልጸዋል ። በዚህ ደረጃ መመለስ ያለበት ጥያቄ የቀረበው ማስረጃ በእርግጥ አቶ ወ/ገብርኤል የአየለች አባት መሆናቸውን በጽሑፍ መግለጻቸውን በበቂ ሁኔታ ማረጋገጥ መቻል አለመቻሉ ነው ።

ከፍርድ ቤቱ ውሳኔና የትምህርት ቤቱ ጸሐፊ ከሰጡት የምስክርነት ቃል የሚከተሉትን መገመት እንችላለን ።

1/ በመዝገቡ ውስጥ ሠፍሮ የሚገኘው ትክክለኛው መረጃ አየለች ወ/ገብር ኤል መሆኗን ፤

2/ ምዝገባው የተካሄደው የአቶ ወ/ገብርኤል ልጅ ናት ያሏትን አንዲት ልጅን አየለች ወ/ገብርኤል በሚል ስም እንዲመዘግብላቸው ለትምህርት ቤቱ ባለሥልጣን ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት በዚሁ ባለሥልጣን መመ መመዝገቧን [8] እና ፤

3/ አመዘጋገቡም የተመረኮዘው በተለምዶ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ናቸው የተባሉት ሰዎች በመዝጋቢው ባለሥልጣን ፊት በሚሰጡት የቃል መግለጫ ላይ መሆኑን ነው ።

ከላይ ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው ስለመዝገቡ መኖርና ስለይዘቱም ጭምር የፍርድ ቤቱ " እውቀት " የመነጨው ፍርድ ቤቱ የውሳኔዎ አንድያ መሠረት ነው ከሚለው " ከጽሑፉ " ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤቱ ከጻፈው ደብዳቤና የትምህርት ቤቱ ባለሥልጣን ከሰጡት የምስክርነት ቃልም ጭምር ነው ። ከዛው ከ "ጽሑፉ " አየለች ወ/ገብርኤል የሚለው ስም በእርግጥ የይግባኝ ባይዋ እንጂ የሌላ የሞክሼ ኢለመሆኑን እንዲሁም አባት ነው የተባለው ሰው የአየለች አባት ነኝ ብሎ መግለጹንና ምዝገባውም የተካሄደው ይህንኑ ገለጻ አስመርኩዞ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አያውቅም ። በሌላ አነጋገር ማናቸውም አየለችንና አባት ነው የተባለውን ሰው የሚያገናኝ ነገር የፈለቀው ከምስክር የምስክርነት ቃል ከመሆኑም ሌላ በጽሑፍ የሠፈረው " የአባትነት ማወቅ " "ጽሑፍ " እንኳ የተረጋገጠው ጽሑፉን ፍርድ ቤት በማቅረብ ሳይሆን በአንድ መኖሩን በሚገልጽ ደብዳቤ ሲሆን ይዘቱም " የተረጋገጠው " ይኸው ምስክር በሰጠው የምስክርነት ቃል ነው ። በዚህ ሁኔቱ እንግዲህ በግልጽ እንደሚታየው ፍርድ ቤቱ የመዝገቡን መኖር በእርግጥ ስለማያውቅና ይኸው መዝገብ ቢኖርም አየለች ወ/ገብርኤል የተባለውን በብዛት የሚገኝ ስምን ከመጠቀም በቀር ምንም ስለማያረጋግጥ ፍርድ ቤቱ ውሳኔዎ የተመረኮዘው በመዝገቡ ላይ ነው ሲል የሰጠውን ቃል እንዳለ መውሰድ አይቻልም ። በተመሳሳይ ሁኔታ ማናቸውም ልጅንና አባት ነው የተባለውን ሰው የሚያያይዘው ነገር በአንድ ምስክር የምስክርነት ቃል ላይ ተመርኩዞ እያለ " የትምህርት ቤቱን ባለሥልጣን የጠራነው በራሱ በአባትነት ማወቁ ጥያቄ ላይ እንዲመሰክሩ ሳይሆን . . ." የሚለውን የፍርድ ቤቱን አባባል ከብዶት ስጥቶ መውሰድ አይቻልም ።

እስቲ አሁን አጠር ባለ መልኩ የታደሰ ጉርሙ ጉዳይን አስመልክቶ የቀረበውን ማስረጃ እንመልከት ። ከጋንዲ ሆስፒታል ከመጣው መዝገብ ውስጥ የሚገኘው መረጃ እንዲህ ይላል ። " የበሽተኛው ስም ጥሩወርቅ እያሱ ፤ ክፍይ ታደሰ ጉርሙ ፤ ስልክ ቁጥር 152025 ። " 15/5/62 እ. ኤ. አ. የሚለው ቀንና የገንዘብ ተቀባዩ ፊርማ ጭምር በደረሰኙ ላይ ይገኛሉ ። ይህንኑ መረጃ ከሚከተሉት ጋራ አቀና

ጅቶ መመልከት ተገቢ ነው ። የይግባኝ ባዩ ልጅ ነው የተባለው ልጅ ስም ማለትም ሰለሞን በደረሰኙ ላይ አይገኝም ። ሌላው ቀርቶ በሽተኛዋ ሆስፒታል የገባችው ለወሊድ ጉዳይ መሆኑ እንኳ አልተገለጸም ። [9] ጉዳዩ ወሊድን አስመልክቶ ቢሆን እንኳ ደረሰኙ የተወሰደው ልጅ ሰለሞን መሆኑንና እናት የተባለችውም በዚህ ጉዳይ ውስጥ መልስ ሰጭ የሆነችው ጥሩወርቅ እያሱ መሆኗን አይናገርም ። በሌላ አነጋገር ይህ ሁሉ የውሳኔው መሠረት ነው ከተባለው " ጽሑፍ " አይመነጭም ። ይህን ሁሉ ፍርድ ቤቱ አገኘ ቢባልም ያገኘው ቀድሞውኑ መስማት ነበረባቸውካላቸው የምስክሮች ቃል ነው ። ጽሑፉን ሲመለከቱት ሕጻኑን ሰለሞንን አባት ነህ ተባለው ከታደሰ ጉርሙ ጋራ የሚያያይዝ አንዳችም ነገር የለም ። ስለዚህ የፍርድ ቤቱን የሕግ አተረጓጎም ተቀብለን ማናቸውም " ጽሑፍ " ተቀባይነት አለው ብንል እንኳ ደረሰኙም ሆነ መዝገቡ ያረጋግጣሉ የተባለውን ነገር ስለማያረጋግጡ በቂነት የላቸውም ።

በታደሰ ጉርሙ ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የተመረኮዘው የአየለችን ጉዳይ አስመልክቶ በተሰጠው የሕግ አተረጓጎም ላይ ሲሆን ወደፊትም የሚነሱ ጉዳዮች በዚሁ ላይ የተመረኮዙ ይሆናሉ ተብሎ የማይታመንበት ምክንያት የለም ። ስለዚህ ፍርድ ቤቱ በህግ ጥያቄ ረገድ በወሰደው አቋም መጠየቅና መገምገም አስፈላጊ ነው ።

## የፍርድ ቤቱ የህግ አተረጓጎም ።

ፍርድ ቤቱ የጽሑፍ ማስረጃን አስመልክቶ በአንቀጽ 748/1/ ትርጉም መሠረት የወሰደውን የሕግ አቋም ስንተነትን " የተጻፈ ማስረጃ " ወይም በጽሑፍ የቀረበ ማስረጃ የሚሉት ቃላት በህግ ፍልስፍና የተሰጣቸውን ትርጉም መወያየቱ ተገቢ ይመስለናል ።

በጽሑፍ የተደረጉ የሰዎች መግለጫዎች ሁለት ዓይነት ፎርም ሊኖራቸው ይችላል ። እነዚህም የግልና የግል ያልሆኑ ወይም በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች ናቸው ። የፊተኞቹ የሚመለከቱት በሚመለከታቸው ወገኖች ስም በነዚሁ ወገኖች የሚዘጋጁትን ሲሆን የኋለኞቹ ደግሞ የመንግሥት ሠራተኞች መንግሥታዊ ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያዘጋጇቸውን ነው ። [10] በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች ማለት " የግል ያልሆኑ ሰነዶችን በህጉ መሠረት በተጠናቀቁበት ቦታ ከነአስፈላጊው ሥነ ሥርዓት ለማዘጋጀት ሥልጣን ያለው የመንግሥት ባለሥልጣን የተቀበላቸው ናቸው ።" [11] ስለዚህ የተረጋገጡ ሰነዶች ባጠቃላይ ማናቸውም ባለሥልጣን የተቀበላቸው መግለጫዎች ሳይሆኑ በህግ በተለይ የተወሰኑት የተቀበሉዋቸው ናቸው ። በክብር መዝገብ የሠፈሩ ጽሑፎች ለምሳሌ የሚዘጋጁት በክብር መዝገብ ሹማምንት ፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ ውሎችንና ሰነዶችን በሚያጸድቅ መንግሥት ባወቀው አዋዋይ ብቻ ነው ። [12]

በአጠቃላይ ሲታይ [13] የግል ሰነዶች በሚዘጋጁበት ወቅት በጹሐፊው ላይ ከሚጣል የፊርማ ግዴታ ውጪ ምንም ዓይነት ሌላ ሥነ ሥርዓት የለም ። [14] ።

በባለሥልጣን በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ በግል ፊርማ ከተጻፉ ሰነዶች የበለጠ እምነት ስለሚጣል የሁለቱ የአስረጂነት ኃይል ይለያያል ። [15] በባለሥልጣን በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ባብዛኛው እምነት የሚጣለው ሰነዶችን ለማዘጋጀት ሥልጣን የተሰጣቸው ባለሥልጣኖች የሚያዘጋጁዋቸውን ሰነዶች ይዘት ትክክለኛነት በተመለከተ ተጠያቂ ስለሚሆኑ ነው ። [16]

የግልም ሆኑ በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች፣“በቀድሚያ የተዘጋጁ ማስረጃ
ዎች ” የተባሉ ብቸኛ የጽሑፍ ማስረጃ ዓይነቶች ናቸው ። ነገር ግን ይህ ማለት
በተለይ ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች የግል ደብዳቤዎች ፣ ይፋ ያልሆኑ ወረቀቶች ፣ ወዘተ
እንደ ማስረጃ ሊቀርቡ አይችሉም ማለት አይደለም ። እንደዚህ ያሉ ማስረጃዎች
የአስረጂነት ኃይላቸው ለዳኛው ህሊና የተተወ ሲሆን ብዙውን ጊዜም የሚያገለግ
ሉት ማስረጃ ለማቅረብ በመንደርደሪያነት ብቻ ነው ። እንደዚህ ያሉት ጽሑፎች
ከላይ የተጠቀሱት ሰነዶች ከሚገኙበት ምድብ ውስጥ ስላይደሉ” ህጉ የጽሑፍ ማስ
ረጃን በሚጠይቅበት ቦታ ዋጋ እንደሌላቸው ይቆጠራሉ ። [17]

እንደገና ለመግለጽ ያህል ህጉ የጽሑፍ ማስረጃ ሲጠይቅ በቅድሚያ የተዘ
ጋጀ ማስረጃን ማለትም ወደፊት አለመግባባት ሲፈጠር ለማስረጃነት እንዲያገለ
ግል ሆን ተብሎ የተዘጋጀን ጽሑፍ ማለቱ ነው ። የጽሑፉ ማስረጃ በባለሥልጣን
በተረጋገጠ ሰነድ ፎርም እንዲሆን ከተጠየቀ ይኸው ጽሑፍ በሌላ በማንም የአስተ
ዳደር ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን ሳይሆን እነዚሁኑ መግለጫዎች እንዲቀ
በሉ በተለየ በተሰየሙ የመንግሥት ባለሥልጣኖች መዘጋጀት አለበት ። የግል ሰነ
ዶች በተጠየቁ ጊዜ ምንም እንኳ በሌላ በሶስተኛ ሰው ቢዘጋጁም በጽሑፉ ባለቤት
መፈረም አለበት ። [18] ስለዚህ ከነዚህ ከሁለት ፎርሞች በአንደኛውም ያልተዘጋጀ
ጽሑፍ ዋጋ ያለው የጽሑፍ ማስረጃ ባለመሆኑ በህጉ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችል
ም ። ከዚህም ተነስተን መደምደም የምንችለው ፍርድ ቤቱ ባጠቃላይ ማናቸውም
የመንግሥት ባለሥልጣኖች መግለጫዎችን ወይም አባት ነው የተባለው ሰው ለማ
ናቸውም መሥሪያ ቤት ያቀረበውን ማመልከቻ አስመርኩዞ የወሰዷቸውን ጽሑፎ
ችና ቃለ ጉባኤዎች እንዲሁም የግል ደብዳቤዎችንና ሌሎች በዛው ሰው የተጻፉ
ጽሑፎችን ዋጋ እንዳላቸው የአባትነት ማወቅ ማረጋገጫዎች ሲቀበል ስህተት
መፈጸሙን ነው ።

ከመለፋቱ የተነሳ የሆስፒታል ደረሰኙን እንኳ ለመቀበል የበቃበት የፍርድ
ቤቱ አተረጓጎም የተመሠረተው እንደሚከተለው በሚነበበው አንቀጽ 747/2/ ላይ
ነው ። “ ይህም የሚሰጠው ቃል አባትነት ማወቅ የሚያስከትለው ውጤት እንዲ
ኖረው ሲል የተናገረ መሆኑ አስፈላጊ አይደለም ። ” ፍርድ ቤቱ የአየለች ጉዳይ
አስመርኩዞ በዚህ አንቀጽ ትርጉም ነው ብሎ የወሰደው በሚከተሉት ቃላት ይገ
ልጻል ።

> “ አንድ መግለጫ የግድ አባትነትን ማወቅ የሚያስከትላቸውን ውጤ
> ቶች ለማምጣት የተደረገ መሆን የለበትም ተብሎ ከተደነገገ አባትነትን
> ለማወቅ ሳይሆን ለሌላ ምክንያት የተዘጋጀ ጽሕፈት በምስክሮች መረጋ
> ገጥ የለበትም ። የግል ደብዳቤ እዚህ ላይ በግልጽ ምሳሌነት ሊያገለግ
> ለን ይችላል ። ”

“ ይኸው ጽሕፈት . . . አባትነትን ለማወቅ ሳይሆን ለሌላ ምክንያት ተብሎ
ሊዘጋጅ ይችላል ። ” ከሚለው ተገቢ መደምደሚያ ፍርድ ቤቱ አንድ ጽሕፈት ዋጋ
እንዳለው የአባትነት ማወቅ ለመቆጠሩ “ የግል ደብዳቤ . . . በግልጽ ምሳሌነት
ሊያገለግለን ይችላል ” ወደሚለው መደምደሚያ ይዘላል ። ፍርድ ቤቱ እንደዚህ
በመደምደሙ በህግ የተጠየቀውን የማስረጃ ፎርም አንድ ሰው በታዘዘው ፎርም
መሠረት ጽሕፈቱን ሲያዘጋጅ ማሟላት ካለበት ሥነ ሥርዓት (ፎርማሊቲ) ጋር
አምታትቶታል ። በሌላ አነጋገር ፍርድ ቤቱ የሥነ ሥርዓት ጽንስ ሃሳብ ከፎርም

ጽንስ ሃሳብ አልለየውም ። ፍርድ ቤቱም የሚከተሉትን የህግ አርቃቂውን ቃላት የአየለችን ጉዳይ አስመርኩዞ መጠቀሙም ለዚሁ ማረጋገጫ ነው ።

> ምንም እንኳ አባትነትን ማወቁ በአንድ በተወሰነ ሥነ ሥርዓት (ፎርማሊቲ) መደረግ ቢኖርበትም የአባትነት አቀባበል ለማናቸውም ልዩ ፎርም ተገዥ አይደለም ። (ለማትኮር የተሠመረው ተጨማሪ ነው ። መ. ገ. ሕ.)[19]

በእግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 103 የዚሁ የሬኔ ዳቪድን ጽሑፍ ተርጓሚ እንዲህ ይላል ።

> በእዚህ አንቀጽ ውስጥ በቀደምትነት የቀረበው ረቂቅ የአባትነት መግለጫ በአራት ምስክሮች ፊት እንዲሰጥ ይጠይቅ ነበር ። በኮሚሽኑ የተሻሻሉት አንቀጽ 747 እና ይህንን ጥያቄ አይዙም ።[20]

" አባትነትን መቀበል " የሚያመለክተው በአንቀጽ 751 እንደተደነገገው በእናትየዋ ወይም እሷ ካልቻለች በሷ ምትክ ወደላይ በሚቆጠሩ ዘመዶች የሚደረገውን የአባትነት መቀበል ነው ። የአባትነቱ መቀበል የግድ ልዩ ፎርም እንዲኖረው ካለማስፈለጉ ሌላ እንዳውም በዝምታ ማለትም " ይህንኑ የአባትነት ማወቅ ካወቀበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተቃውሞውን ባለማንሳት "[21] ሊሆንም ይችላል ። ይሄም አንቀጽ 748 1/ " አንድ የአባትነት ማወቅ በጽሑፍ ካልቀረበ ዋጋ አይኖረውም " ብሎ አጥብቆ ከሚያዘውና ከሚጠይቀው የተለየ ነው ። ( ለማትኮር የተሰመረ ) የተጨመረውም ዓይነት ፎርም ሊደረግና በማናቸውም ዓይነት ዘዴ ለምሳሌ በግል ደብዳቤ ሊረጋገጥ ይችላል ።[22] ፍርድ ቤቱ ማናቸውም ዓይነት ፎርም ያለው የጽሑፍም ሆነ የቃል ማስረጃ ከመቀበል አይከለከልም ።

ዳቪድ የአባትነት ማወቅን አስመልክተው በሚጠቅሱበት ጊዜ የሚጠቀሙት ፎርሙን ሳይሆን (በእርግጥም ፎርሙ በጽሑፍ መሆን ስላለበት) የተርጓሚው ማብራሪያ እንደሚያመለክተው በህግ አርቂቂው ኮሚሽን በኋላ የተዘለለውን በአራት ምስክሮች ፊት የማረጋገጥ ጥያቄን የሚጠቁመውን " አንድ ዓይነት ሥነ ሥርዓት (ፎርማሊቲ) " ነው ። የተጠየቀው ፎርም የጽሑፍ ማስረጃ ለምሳሌ የግል ሰነድ ከሆነ በምስክሮች የማረጋገጡ ሥነ ሥርዓት ሥር ሊወድቅም ላይወድቅም ይችላል ። ለምሳሌ ውሎች በጽሑፍ እንዲደረጉ በታዘዘበት ቦታ የግድ በምስክሮች መረጋገጥ የለባቸውም ። ይኸው አባባል ኑዛዜን በተመለከተም ትክክል ሲሆን አባትነት ማወቅን በተመለከተ ግን ቅድም እንደተገለጸው ትዕዛዙ በኮሚሽኑ ተቀባይነት ስላጣ ትክክለኛ አይሆንም ። ስለዚህ ፍርድ ቤቱ የፎርሙን ጥያቄ ሥነ ሥርዓት (ፎርማሊቲ) አስመልክቶ ከተደነገገው ጋራ በማምታታቱ ከህጉ መንፈስና ድንጋጌ እንዲሁም ከህሊና ግምት ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ አባትነት ማወቅን በእናት አባትነትን ከመቀበል ጋራ በአንድ ደረጃ አስቀምጧቸዋል ።

እርግጥ አንድ ዋጋ ተሰጥቶት ሊነሳ የሚችል ክርክር ቢኖር አንቀጽ 748 2/ የአባትነት ማወቅ በክብር መዝገብ ሹማምንት ወይም እነሱ ከሌሉ ውሎችንና ሰነዶችን በሚያጸድቅ መንግሥት ባወቀው አዋዋይ ፊት መደረግ እንዳለበት የሚጠቀመውን ግምት ውስጥ በማስገባት በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች ብቻ እንደ አባትነት ማወቅ እንዲቆጠሩ የሚለው አቋም ነው ።

ከዚህ በላይ ያለውን አባባል ከፈረንሳይ የአባትነት ማወቅ ህግ ጋራ በማመሳከርም ጭምር መመልከት ይቻላል ። በፈንንሳይ ሕግ አባትነትን ማወቁ በባለሥ

ልጣን በተረጋገጠ ሰነድ ፎርም እንዲሆን ሲጠየቅ በግል ጽሑፍ የሰፈረ መግለጫ ፈጽሞ ተቀባይነት የሰውም [24] በፕላኒዎል ቃልም እንደተገለጸው [25]

> ሕጉ ምንም ዓይነት ምስጢር አዘል የሆነ ፎርማሊቲ አያዝም ። የአባትነት ማወቁ የሠፈረበት በመንግሥት የታወቀው ሰነድ አጽዳቂው ሰው ጽሑፍ እንኳ ቢሆን ይሄንኑ ማወቅ በተለይ ለመቀበል ተብሎ የረቀቀ መሆን የለበትም ። በአባትነት ማወቁ ባጋጣሚ እንዳውም በውስጠ ታዋቂነት ጭምር በሰነዱ ውስጥ ሊገኝ ይችላል ። . . . ስለዚህ የአባትነት ማወቁ ጽሑፍ የተጻፈበት ዋና ዓላማ አካል ሳይሆን በሰነዱ ውስጥ ከሠፈሩ የሀሳብ መግለጫዎች ብቻ ሊመነጭ ይችላል ።

ከላይ ከተጠቀሰው በግልጽ እንደሚታየው ምንም እንኳን የፈረንሳይ ሕግ የአባትነት ማወቅ በባለሥልጣን በተረጋገጠ ጽሑፍ እንዲደረግ ቢጠይቅም በአንቀጽ 747 (2) ውስጥ የተደነገገውና በፈረንሳይ ሕግ የተደነገገው አንድ ዓይነት ነው ። ስለዚህ የአባትነት ማወቁ ውሎችንና ሰነዶችን የሚያጸድቅ መንግሥት ባወቀው አዋዋይ የሚዘጋጅ ሰነድን ፎርም ከያዘ ኑዛዜ ወይም ምንም እንኳ የሰነዱ ዓላማ “ የአባትነት ማወቅ የሚያስከትላቸው ውጤቶች ከመፍጠር ውጪ ” ቢሆንም ከማናቸውም ዓይነት በባለ ሥልጣን የተረጋገጠ ሰነድ ሊፈልቅ ይችላል። እንግዲህ አንቀጽ 747 /2/ መተርጐም ያለበት ባጠቃላይ ማናቸውንም ዓይነት አባት ነው በተባለው ሰው በጽሑፍ የሠፈሩ መግለጫዎችን እንደሚፈቅድ ሳይሆን ሰነዱ የተዘጋጀው በቅድሚያ በተዘጋጀ ማስረጃ ፎርም ማለት በባለሥልጣን በተረጋገጠ ሰነድ ወይም ተጽፎ በተፈረመ ሰነድ ፎርም ከሆነ መግለጫው እንዴት እንደተደረገ እንዳችም ሥነ ሥርዓት እንደማይጠይቅ ነው ።

## መደምደሚያ ፤

ፍርድ ቤቱ ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ልጆች ያለአባት መቅረት የለባቸውም ከሚለው ትልቅ ዋጋ ከሚሰጠው ሃሳብ ተነስቶ የትምህርት ቤት መዛግብት ፥ የሆስፒታል ደረሰኞችና የግል ደብዳቤዎች ዋጋ እንዳለቸው የአባትነት እውቅናዎች በመቁጠሩ ከሚገባው አልፎአል ። እንደዚህ ያለውን አቋም መውሰድ የአንቀጽ 748/2ን ዓላማ ማለትም እንደማያስተማምን በይፋ በታወቀው የሰው ማስታወስ ላይ ከተመሠረተው የምርስክሮች የምስክነት ቃል ይበልጥ አስተማማኝ የሆነ የማያጠራጥር ማስረጃን በቅድሚያ ማዘጋጀትን ተጻሯል ። እዚህ ላይ በእርግጥ አንድ ሰው በመሐላ የተሰጠው የምስክሮች ቃላትን በታደሰ ጉርሙ ጉዳይ ዋጋ አለው ተብሎ እንዲቀርብ ከተፈቀደው ደረሰኝ ያነሰ አስተማማኝነት አላቸው ማለት ያስደፍራልን ? አይመስለኝም ። ፍርድ ቤቱ የግል ወይም የግል ባልሆኑ ሰነዶች መልክ “ በቅድሚያ የተዘጋጁ ማስረጃዎች ” ብቻ በመፍቀድ ራሱን መወሰን ነበረበት ።

የፍርድ ቤቱን የህግ አተረጓጐም ትክክለኛ ነው ብንል እንኳ ፍርድ ቤቱ የራሱን የህግ አተረጓጐም ሳያዛንፍ ተከትሎ በነዚህ በሁለት ጉዳዮች ጽሑፍን (ጽሑፍ ስንል በተለምዶው አነጋገር ያለውን ትርጉም ነው ) ብቻ እንደማስረጃ አለመቀበሉና በእርግጥም ይበልጥ የተማመነው በምስክሮች የምስክርነት ቃል ላይ መሆኑ ግልጽ ነው ። ፍርድ ቤቱ በእርግጥ በተጨባጭ በማናቸውም ፎርም የቀረበን ማስረጃ ሲቀበል ራሱን በጽሑፍ በቀረበ ማስረጃ አልወሰነም ። ፍርድ ቤቱ የወሰደው አቋም ከህጉ ድንጋጌም ሆነ መንፈስ ከረር ባለ ሁናቴ የተለየ ሲሆን ይኸው አቋም በፍርድ ቤቱ የተገለጸው ጥንቃቄ የሞላበት ሀሳብ ሳያግደው ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ወደነበሩበት ሁናቴዎች በተግባር መመለስ ማለት ይመስላል ።

## የግርጌ ማስታወሻዎች ።

ሌክቸረር ፣ የሕግ ፋኩልቲ ፣አ. አ. ዩ. ኤል ቢ ፣ የሕግ ፋኩልቲ አ. አ. ዩ.

1. ለግምግማ የቀረቡት ሁለቱ ጉዳዮች ከአሁን በኋላ “ የአየለች ጉዳይ ” እና “ የታደሰ ጉርሙ ጉዳይ ” በመባል ይታወቃሉ ።
2. በዚህ ጉዳይ ውስጥ አንቀጾች ሁሉ የተጠቀሱት ከ1952 የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ነው ።
3. አንቀጽ 748/1 እንደሚከተለው ይነበባል “ የአባትነት ማወቁ በጽሑፍ ካልሠፈረ በቀር ውጤት አይኖረውም ። ”
4. “ ጸሐፊ ” የሚለው የሰነዱን አዘጋጅ ይጠቁማል ።
5. መሥሪያ ቤት የሚለው ቃል የግል መሥሪያ ቤቶችንና ሕዝባዊ ድርጅቶችን ይጨምር ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤት ይወሰን ግልጽ አይደለም ።
6. ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ ንባብ እንደሚታየው በኢትዮጵያ እንደተለመደው ክርክሩ የተነሳው ይግባኝ ባይዋ በእናትዋና በአሳዳጊዋ በኩል በአንቀጽ 996 ትርጉም መሠረት እንደ አቶ ወ/ገብርኤል ወራሽ “ የወራሽነት የምስክር የምስክር ወረቀት ” እንዲሰጣት በጠየቀች ጊዜ ነበር ።
7. ፍርድ ቤቱ ዙሪያ ጥምጥም በመሄድ የፈለገውን ነጥብ ከማረጋገጥ ይልቅ ለምን መዝገቡን እራቱ ለምርመራ እንዳላቀረበ ግልጽ አይደለም ።
8. አቶ ማርቆስ በአቶ/ ወ/ገብርኤል ተገለጸ የተባለውን መግለጫ የተቀበለው ሰው ይሁን አይሁን ከጉዳዩ ግልጽ አይደለም ።
9. ጋንዲ ሆስፒታል የማዋለድ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የማኅፀን በሽታዎችን ባጠቃላይ ስለሚመለከት ደረሰኙ ከሆስፒታሉ መምጣቱ ምንም አይጠቅምም ።
10. ፕላኒዎል ፣ ትሬት ኤሌሜንቴር ድሮ ሲቪል ፣ /ፓርት/ ፣ 1939/ ገጽ 235—6
11. ፕላኒዎል ፣ እላይ የተገለጸው ፤ ቮል 2 ፤ ፓርት 1 ፤ ገጽ 53 በዛው ገጽ ላይ ፕላኒዎል የሚከተለውን በተጨማሪ ይገልጻሉ ፤ “ በባለሥልጣን ከተረጋገጡ ሰነዶች ጋራ ተዋህደው ይታያሉ ። ” እንደገና እንዲህ ይላሉ “ የአስተዳደር ወኪሎች ብዙ በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች ያዘጋጃሉ ። ነገር ግን ፣ ማረጋገጫ የሚሰጡት በሥልጣናቸው ወሰን ሥር ለረቀቁት ብቻ ነው ። ” ፕላኒዎል ፣ በማስታወሻ ቁጥር 10 እላይ የተጠቀሱት ፣ ገጽ 806 ፤
12. ከአንቀጽ 48 እና 146 ጋር አስተያዩ ። የፈረንሳይ ሕግ በአባትና እናት ማወቅ ጊዜ በማሃላ በፍርድ ቤት ፊት ተሰጥቶ በፍርድ ቤቱ ጸሐፊ ለተመዘገበ የምስክርነት ቃል በባለሥልጣን የተረጋገጠን ጽሑፍ ደረጃ ይሰጠዋል ። ፕላኒዎል ፣ ቮል 1 ፣ ፓርት 1 ፣ በማስታወሻ ቁጥር እላይ የተጠቀሱት ፣ ገጽ 806—7
13. በአንቀጽ 831 እና 1727 ከተጠቀሱት በምስክሮች መረጋገጥ ካለባቸው የግል ሰነዶች ጋር አስተያይ ።
14. “ ፊርማው ለጽሑፉ የማስረጃ ኃይልነት ይሰጠዋል ። ፊርማ ያልሰፈረበት ጽሑፍ እንደ ጽሑፍ ማስረጃነት ከፍትሐብሔር ጉዳዮች እንኳ በመንደርደሪያነት ዋጋ አይኖረውም ። ፕላኒዎል ፤ በማስታወሻ ቁጥር 11 እላይ የተገለጹት ፤ ገጽ ፣ 531 ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሳይሆን ሰነዱ የባዕድ ጽሑፉን ባዘጋጀው በራሱ በጸሐፊው መዘጋጀት የለበትም የሚለው ነጥብ በጥልቀት መርምሮታል ። ” እነሱ (ማለትም የግል ጽሑፍ ጸሐፊዎች መ. ፕ. ሕ.) በሌላ በሶስተኛ ሰው የተዘጋጀውን ጽሑፍ በመፈረም ብቻ ሊወስኑ ይችላሉ ። ” ከዚያው ፤ ገጽ 43 ። በተጨማሪም አንቀጽ 88/1/ ፣ 1728 እና 1728 እና 1720 ን ነዛዜን ውሎችንና ፎርምን ተመልከቶ በተከታታይ የተደነገገውን ተመልከት ።
15. “ በግል ፊርማ የተጻፉ ሰነዶች ” የሚባሉት በአብዛኛው “የግል ሰነድ” ከሚለው ጋራ ተመሳሳይ ትርጉም ስለሚሰጣቸው የጸሐፊው ፊርማ ሊቀር የማይችል መሆኑን ያሳያሉ ።
16. አንቀጽ 143 ተመልከት ።
17. ፕላኒዎል ፤ ቮል 2 ፤ ፓርት 1 ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሱት ፤ ገጽ 556—566 ።
18. ፊርማው በጽሑፍ ይሁን ወይም በአውራ ጣት ምልክት ወይም በሌላ ማናቸውም መልክ የተደረገ ቢሆንም ፊርማው በአስተማማኝ ሁኔታ ማረጋገጥ ከተቻለ የፊርማው ጠባይ ግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም ።
19. ዴቪድ ፤ አር ፤ “ ዘ. ፋሚሊ ሎው ኢን ኢትዮጵያን ሲቢል ኮድ ” በአዶኖባን ኬ ፤ ያልታተመ ገጽ 97 ።
20. ዴቪድ ፤ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 19 የተጠቀሱት ገጽ 27 ።
21. አንቀጽ 753 ።

22. ከጋብቻ ውጪ የተወለደን ልጅ እናትነት ብቻ መመሥረት በሚቻልበት በፈረንሳይ አገር እንኳ መወለድ ብቻ በቂ እንደሆነበት እንደ ኢትዮጵያ ሳይሆን በአባትነት ማወቁ በቅድሚያ በይፋ ከተደረገ በእናትየዋ የተደረገው የአባትነት መቀበሉ በግል ደብዳቤ ሊሆን ይችላል ።

23. የፍትሐብሔር 1ኛ መጽሐፍ ቻፕተር 3 ተመልከት ።

24. ፕላኒዎል ፤ ቮል 1 ፓርት 1 ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 1 የተገለጹት ፤ ገጽ 808 ።

25. ከዛው ፤ ገጽ 807—808 ።